30

H1-85200250/36
21/2/2006

**726/2013**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development & Construction

ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ

ከ/ል/ኮ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡- የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ፤

የ5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት የከተሞች ራስን የማስተዋወቅ ውድድር መመሪያ ቁጥር 30/2005 ሆኖ ከጳጉሜ 5 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የፀደቀ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሠረት መመሪያውን እንድታስፈጽሙ የፀደቀው መመሪያ 1 ጥራዝ ሰነድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን እየገለጽን የሰነዱ ግልባጭ የተመዘገበላችሁም እንድትከታተሉት እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም
ሚኒስትር

ግልባጭ፡-

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (ከተማ ልማት ዘርፍ)
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (ኮንስትራክሽን ዘርፍ)
- ለሀብት ሥራ አመራርና ማስተባበሪያ ቢሮ
- ለህግ አገልግሎት መመሪያ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት አብይ ኮሚቴ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት ቴክኒክ ኮሚቴ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት የፓናል ውይይት ዝግጅት ኮሚቴ

ከ/ል/ኮ/ሚ/ር

21/02/06

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND CONSTRUCTION

# ፫ኛው የኢትዮጲያ ከተሞች ሣምንት የከተሞች ራስን የማስተዋወቅ ውድድር

## መመሪያ ቁጥር 30/2005

የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት
ETHIOPIAN CITIES WEEK

ባህር ዳር
Bahir Dar

## 1. -መግቢያ

በኢትዮጵያ ፈጣን የከተሞች መስፋፋትን ተከትሎ የከተማ ነዋሪዎችንና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማጠናከር መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በማስፋፋት የከተማ ልማት ፖሊሲውን እና የከተማ ልማት ኘሮግራሞችን ትግበራና ስኬት ማፋጠን ይቻል ዘንድ አመታዊ የከተሞች ሣምንት የተሰየመ ሲሆን የኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት በተለያዩ ከተሞች አስተናጋጅነት በየዓመቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንደሚከበር ይታወቃል።

ከኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት አበይት ክንውኖች መካከል ከተሞችን መንግስት በነደፋቸው ስትራቴጂዎች አፈፃፀምና ያከናወኗቸው ተግባራት ከበኣሉ ተሳታፊዎች ጋር ራስን የማስተዋወቅ ሥራ አንዱ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ከተሞች በአለፉት ዓመታት በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ከፍተኛ እድገት ያስመዘገቡበትና ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት የሚሰጡት ግብዓት ከፍ ያለበት ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን ይህም ከተሞች ለኢንቨስትመንት፣ ለገበያ፣ ለቱሪዝም ወዘተ በራቸውን እርስ በእርስ ብቻ ሳይሆን ከዓለም ከተሞችም ጋር ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ውድድር ከተሞች እድገታቸውን ለማፋጠንና የኗሪዎቻቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ ከ 726/2013 በተጨማሪ ብቃት ያለው ራስን የማስተዋወቅ (Professional City Marketing) ስራን የሚጠይቅ ነው። ስለዚህም ከተሞች ከመቼውም ይበልጥ የተደራጀና ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃን በጠበቀ መልኩ ራሳቸውን የማስተዋወቅ እና የመሸጥ ሥራን አጠናክረው ማከናወን ይጠበቅባቸዋል። የኢትዮጵያ ከተሞች ሣምንት ይህንን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የከተሞቻችንን ራስን የማስተዋወቅ ሥራ ለማገዝ ይቻል ዘንድ ሀገር አቀፍ የኢትዮጵያ ከተሞች ኤግዚቢሽን በኘሮግራሞቹ አካቷል።

በመሆኑም ይህንን የከተሞች ራስን ማስተዋወቅ ሥራ ይበልጥ ለማጎልበት በውድድር መልክ እየተዘጋጀ የላቀ ደረጃ እንዲደርስ መደረግ አለበት። ከዚህ አኳያም ከተሞች በዘርፉ በተለዩ ሰባቱ ዓምዶች (በስራ ዕድል ፈጠራ፣ በመሬት ልማት ማኔጅመንት፣ በከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ፣ የመኖሪያ ቤቶች ልማት፣ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ፣ የከተሞች መሠረተ ልማት አቅርቦትና ስራ አመራር፣ በከተሞች ፕላን፣ ፅዳትና ውበት አፈፃፀም አንፃር ያላቸውን ምቹ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ሲስተዋውቁ ውድድሩን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል መስፈርት ለማዘጋጀት ይቻል ዘንድ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል።

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የከተሞች ራስን የማስተዋወቅ ውድድር መመሪያ ቁጥር 30/2005 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) «ከተማ » ማለት የህዝብ ብዛታቸው ከ2000 በላይ የሆነ በክፊል ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፎች ተልዕኮን በማሳካት ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ ያበረከቱ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት፣ የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት፣ የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች ምክር ቤት አባል ተቋማት እና የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተባባሪ ድርጅቶች ናቸው፣

2) «ከተማን ማስተዋወቅ» ማለት ከተሞች በሰባቱ ኣምዶች የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች አፈጻጸም እና ለኢንቨስትመንት ያላቸውን አማራጮች ለከተማው ህዝብ እና ለልማት አጋሮቻቸው በኤግዝቢሽኑ በአካል በመሳተፍ ራሳቸውን ማስተዋወቅ ማለት ነው፣

3) «ፈርጅ» ማለት ለዚህ ውድድር ሲባል ከተሞች ለጊዜው ተመድበው የሚወዳደሩበት ምደባ ነው፣

4) «ዳኞች» ማለት ለዚህ ውድድር ሲባል በአብይ ኮሚቴ የሚሰየሙ በከተሞች ደረጃ የሚደረገውን ውድድር የሚዳኙ ባለሞያዎች ናቸው

5) «መረጃ» ማለት በውድድሩ ጊዜ የሚቀርቡ የፅሁፍ፣ቻርቶች፣ፎቶ ግራፎች እንዲሁም ተንቀሳቃሽ ፊልሞችንም ይጨምራል

6) «ሚኒስቴር» ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ማለት ነው፣

7) «ክልሎች» ማለት በኢትዮጵያ ፌ/ዲ/ሪ/ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 ሥር የተመለከቱ ዘጠኙን ክልሎች ሲሆን ለመመሪያው አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባና ድሬዳዋ አስተዳደሮችን ያጠቃለለ ነው፡፡

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው በ2006 ኣ.ም ለሚከበረው 5ኛው የከተሞች ሳምንት ቀርበው በሚወዳደሩ ከ2000 ህዝብ ያላቸው ከተሞች ላይ ነው፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

1) ከተሞች የልማት ስራዎቻቸውን የሚያሳዩበት፣ እርስ በእርስ የሚማማሩበት፣ ለነዋሪዎቻቸውና ለባለድርሻ አካላት አስፈላጊ መረጃ የሚሰጡበት፣ እንዲሁም የኢንቨስትመንት፣ የቱሪዝም፣ የገበያና የሌሎች መስህቦቻቸውን የሚያስተዋውቁበት መድረክ በመፍጠር አጋዥ የሚሆኑ ግብዓቶች 726/2013 ገኙ ለማስቻል፣እንዲሁም ራሳቸውን በብቃት በማስተዋወቅ የእርስ በርስ ጤናማ የውድድር መንፈስ ለማዳበር የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የከተሞች ራስን ማስተዋወቅ ውድድር

## 5. የውድድር ፈርጆች

ተወዳዳሪዎች በ 2005 ዓ.ም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተሞችን ፈርጅ ለመለየት በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት በአምስት ፈርጅ ተከፍለው የሚወዳደሩ ሲሆን ውድድሩን ፍትሃዊ ለማድረግ የከተሞች መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ተጠቃሚ ከተሞች ከሁሉም ደረጃዎች ወጥተው ለብቻቸው ይወዳደራሉ፡፡

| ተ.ቁ | ቡድን | የህዝብ ብዛታቸው | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| 1 | አንድ | ከ100,001 በላይ | |
| 2 | ሁለት | 50,001-100,000 | |
| 3 | ሦስት | 2,001- 50,000 | |
| 4 | አራት | ULGDP | በULGDP ተሳታፊ የሆኑ 19 ከተሞችን የሚያካትት ነው፡፡ |

## 6. የውድድር ይዘት

1) በውድድሩ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ የዘርፉ ዓምዶች

ከተሞች ራስን ለማስተዋወቅ ውድድር መነሻ የሚያደርጉት በዘርፉ የተለዩትን ዓምዶች/Pillars/ አፈፃፀም ለህዝብ፣ ለልማት አጋሮች ማሳወቅ መሠረት ያደረገ ሲሆን ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

ሀ. በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስራዎች

ሐ. የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ስራዎች

ሐ. የከተማ መሬት ልማትና ማናጅምነት ስራዎች

መ. የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ሕንፃዎች ግንባታ ስራዎች

ሠ. የከተሞች መሠረተ ልማት አቅርቦትና ማኔጅመንት ስራዎች

ረ. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪና ሬጉላቶሪ ስራዎች እና

ሰ. የከተማ ፕላንና ፅዳትና ውበት ስራዎች ናቸው፡፡

2) <u>የመረጃው ይዘት</u>

የሴክተሩን ዋና ዋና ሥራዎች በተለይም የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የመልካም አስተዳደር፣ መሬት ልማትና ማኔጅመንት፣ የመኖሪያ ቤት ልማት፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ፣ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አጠቃቀም፣ የመሠረተ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥ፣ ወዘተ እንደዚሁም ለኢንቨስትመንት የተዘጋጁ ምቹ ሁኔታዎች፣ የነዋሪው ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት፣ የቱሪዝም መስህቦት፣ ወዘተ ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባዋል፡፡

3) <u>የመረጃ ዝግጅትና አቀራረብ፤</u>

1) በጽሑፍ የሚቀርቡ መረጃዎች በግልጽ የሚነበቡ እና ግድፈት የሌለባቸው መሆን አለባቸው፣ በተጨማሪም በእጅ ያልተጻፉ እና ባለቀለም መሆን አለባቸው፤

2) የመረጃ ቻርቶች ባለቀለም፣ በግልጽ የሚታዩ፣ በእጅ ያልተዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል፣ በሚታይ ሁኔታ መሰቀል አለባቸው፣ የቻርቶቹ መጠን ከA3 መጠን ያላነሰ መሆን አለበት፤

3) ፎቶግራፎች በጥራት የተነሱ ገላጭ እና ለእይታ አመቺ መጠን ያላቸው መሆን ይገባቸዋል፣ ለኤግዚቢሽን የሚቀርቡ የፎቶግራፎች መጠን ከA4 መጠን ያላነሰ መሆን አለበት፤

4) <u>ለጎብኚዎች የሚደረግ ገለጻ</u>

1. ጎብኚዎችን ለመሳብ የተለያዩ የማስተዋወቂያ ዘዴዎች አጠቃቀም፤

2. አጠር ባለ ጊዜ በቂ መረጃ መስጠት መቻል፤

5) <u>የድምፅ አጠቃቀም</u>

1) ኤግዚቢሽኑን ብሎም ሌሎች የኢትዮጵያ ከተሞች ዝግጅቶችን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ይቻል ዘንድ የበዓሉ ቦታ ለመደማመጥና መገለጫዎችን በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት ምቹ መሆን አለበት፤

2) ቲሳታፊዎች የሚጠቀሙባቸው እንደ ሙዚቃ፣ የቴሌቪዥን ማስታወቂያዎች፣ ፊልሞች፣ መግለጫዎች ወዘተ የመሳሰሉት ድምፅ የሚያወጡ ግብአቶች በአካባቢያቸው ያሉትን ሌሎች ተሳታፊዎች የማያውክ ሁኔታ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፤

## 7. የውድድሩ ዳኝነት እና ሂደት

1) የዳኞች አመራረጥ በስነ-ምግባራቸው፣ ታማንነትና ብቃታቸው፣ ባለፉት አመታት ባላቸው ተሳትፎና አፈፃፀም መሠረት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከፌደራል ተጠሪ ተቋማት እና ሌሎች ሚኒስቴር መ/ቤቶች እንዲሁም የሚዲያ ባለሞዎች የሚካተቱበት ይሆናል፤
2) ዳኞች በዓብይ ኮሚቴ የሚሰየሙ ሲሆን ማንነታቸውም እስከ ውድድሩ ማጠቀለያ ድረስ በይፋ አይገለጽም፤
3) የከተሞች ራስን ማስተዋወቅ ዝግጅትን ለማወዳደር ለተመረጡ ዳኞች ገለጻ ይደረጋል፤
4) የዳኞች ቡድን አባላቱ በውድድር መስፈርቶች ላይ በመወየየት የጋራ ግንዛቤ ይይዛል፤ የውድድሩ መስፈረርችና ለየመስፈርቱ የሚሰጠው ከፍተኛ ነጥብ በዚህ የውድድር መመሪያ ላይ የተገለጸው ይሆናል፤
5) የዳኞች ቡድኖች የየራሳቸውን ሰብሳቢ ይመርጣሉ፣ ሰብሳቢዎቹም በቀጣይ የዳኞች ቡድኖቹ የሚያደርጉዋቸውን ስብሰባዎች እንዲሁም የውድድሩን ሂደት ይመራሉ።
6) ሶስቱ ዳኞች ቡድን ከኢትዮጵያ ከተሞች መክፈቻ ጀምሮ በበአሉ አከባበር ወቅት የተሳታፊ ከተሞች ኤግዚቢሽን እየተዘዋወሩ ይጎበኛሉ፣ ሆኖም የጉብኝት ኘሮግራማቸው በተወዳዳሪ ከተሞች መታወቅ የለበትም፤
7) የዳኞች አባላት እንደ ስምምነታቸው በጋራ ወይም በተናጥል የከተሞችን ዝግጅት ሊጎበኙ ይችላሉ፤
8) የዳኞች ቡድን አባላቱ በየእለቱ ማጠቃለያ እየተገናኙ ስለቀኑ ውሎአቸው፣ በእለቱ ስለሰጡዋቸው ነጥቦች እና ነጥቦቹን ስለሰጡበት ምክንያት እንዲሁም ስለውድድሩ አጠቃላይ ሂደት ይወያያሉ፤
9) በኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ማጠቃለያ ዋዜማ የዳኞች ቡድን አባላት በየቡድናቸው ይገኛሉ፣ እያንዳንዱ አባል ለገመገመው ከተማ የሰጠውን ውጤት በውጤት መመዝገቢያው ላይ በግልጽ በመጻፍ እና ፎርሙ ላይ ፊርማውን በማስፈር ያስረክባል፤
10) በአባላት መሃከል የሀሳብ ልዩነት ቢፈጠር በተቻለ መጠን ለመግባባት ሙከራ ይደረጋል፤ ካልሆነ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፤
11) የዳኞች አማካይ ውጤት ተደምሮ ከፍተኛውን ውጤት (ከ1ኛ - 3ኛ) ያገኙ ከተሞች ይለያሉ፣ በውጤቱ ላይም የዳኞች ቡድን አባላቱ አስተያየቶቻቸውን ተለዋውጠው የጋራ መግባባት ላይ ይደርሳሉ፤

12)- የውድድሩ አሸናፊዎችን የሚገልጽ ቃለ ጉባኤ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ሲሆን በተጨማሪም በከተሞች ኤግዚቢሽን እና ከተማን የማስተዋወቅ ስራ የታዘቡዋቸውን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች እንዲሁም የማሻሻያ ሀሳቦችን በሪፖርት መልክ ማዘጋጀት ይጠበቃል፣ ይህ ሪፖርትም ከውድድሩ ማብቂያ በኋላ ለተሳታፊ ከተሞች የሚሰጥ ግብረ መልስ ይሆናል፤

13) የዳኞች ቡድኖች አሸናፊዎች በይፋ ታውቀው ሽልማት እስከሚቀበሉበት የኢትዮጵያ ከተሞች የመዝጊያ ስነ ስርዓት ድረስ የውድድሩን ውጤት በሚስጥር ይይዛሉ፤

14) ለአሸናፊ ከተሞች ሽልማት ከተሰጠ በኋላ ንኡስ ኮሚቴው እና ዳኞች በተገኙበት በውድድሩ አጠቃላይ ሂደት እና መሻሻል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ግምገማ ይካሄዳል።

8. <u>የውድድሩ መስፈርቶች</u>

| ተ.ቁ | መስፈርት | የሚሰጠው ከፍተኛ ነጥብ |
|---|---|---|
| 1 | የኤግዚቢሽን አቀራረብ (ከተማው በኤግዚቢሽን መመሪያው የተካተተውን የጥራትና የይዘት መመሪያ መከተሉ) | 30 |
| 1.1 | የቀረቡ መረጃዎች ይዘት | 10 |
| 1.2 | የቀረቡ መረጃዎች ጥራት | 7 |
| 1.3 | የአቀራረብ ቅደም ተከተል | 3 |
| 1.4 | የቻርተሮች፣ ፅሑፎች፣ ፎቶግራፎች ወዘተ አጠቃቀም | 3 |
| 1.5 | የፊልሞች አጠቃቀም | 2 |
| 1.6 | ኤግዚቢሽኑ የከተማውን የልማት እንቅስቃሴ የኢንቨስትመንት የቱሪዝም ወዘተ መስህቦች በሚገባ ማንፀባረቅ መቻሉ | 5 |
| 2 | የጎብኝዎች አቀባበል እና ገለፃ | 25 |
| 2.1 | የገለጻ ሰጪው (ሰጪዋ) በቦታው መገኘት | 5 |
| 2.2 | ገለፃው የፈጀው ጊዜ (በአጭር ጊዜ በቂ መግለጫ መስጠት መቻል) | 5 |
| 2.3 | የገለፃው ይዘት (relevance) | 10 |
| 2.4 | ጎብኚዎች ሲደርሱ በቦታው የነበረው (የነበሩት) የከተማ ተወካዮች ያደረጉት አቀባበል (ሰላምታ፣ ፈገግታ፣ ቅልጥፍና፣ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን)፣ ወዘተ | 5 |
| 3 | የከተማዋ ልዩ መገለጫዎች | 15 |

| | | |
|---|---|---|
| 3.1 | ሎጎ | 5 |
| 3.2 | ሲቲ ብራንድ (ልዩ መገለጫ ስም) | 5 |
| 3.3 | ለጎብኚዎቹ የሚሰጡ የተለያዩ ብሮሽሮች | 2 |
| 3.4 | ለኤግዚቢሽኑ ድምቀት የሚሰጡ ባህላዊ እሴቶች | 3 |
| 4 | **በከተማዋ የሚንቀሳቀሱ የልማት አጋሮችን ለማስተዋወቅ የተደረገ ጥረት** | 20 |
| 4.1 | የጎብኝዎች አስተያየት | 10 |
| 4.2 | የአስተያየት መስጫ መዝገብ መኖር | 4 |
| 4.3 | መዝገቡን የሚያስሞላ ሰው በቦታው መኖር | 3 |
| 4.4 | በመዝገቡ ላይ የሰፈሩ አስተየየቶች ብዛት | 3 |
| 5 | **የድምፅ አጠቀቀም** | 10 |
| 5.1 | ቦታ ለመደማመጥ መገለጫዎችን በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት የሚያስችል ከሆነ | 4 |
| 5.2 | ድምፅ የሚያወጡ ግብዓቶች በአካባቢያቸው ያሉትን ሌሎች ተሳታፊዎች በማያውክ ሁኔታ የሚጠቀም ከሆነ | 6 |

## ክፍል ሦስት

## <u>የመተባበርና የመቀናጀት ሁኔታ</u>

### 9. <u>አሰተባባሪ አካላት</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱት አካላት የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ለማድረግ የከተሞች ሳምንት አዘጋጅ ኮሚቴው ያስተባብራል፣ ያቀናጃል፣

### 10. <u>የመወዳደሪያ ወቅት</u>

እውቅናው በየዓመቱ የሚሰጥ በመሆኑ በእያንዳንዱ ዓመት ለውድድር የሚወሰደው በቀረበው መረጃ ይሆናል፣

## 11. የእውቅና ዓይነትና የሚኖረው ፋይዳ

1) የእውቅናው ዓይነት በሰርቲፊኬትና ተቋማትን መሰረት አድርጎ በሚዘጋጀው ማቴሪያል ይሆናል፣

2) እውቅናው የሚኖሮው ፋይዳ ተሸላሚ ከተሞችን እንደ ሞዴል ከተማ ስለሚታይ ተሞክሮው ተቀምሮ ለሌሎች እንዲሰፋ ይደረጋል፣

## 12. መመሪያው የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ ጳጉሜ 5 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም

የከተማ ልማት፣ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር